**Finote Ethio-Canadian Information Centre In Toronto**
**ፍኖተ ኢትዮ-ካናዳውያን የኢንፎርሜሽን ማዕከል በቶሮንቶ**
25 Norfield Crescent. Toronto. ON. M9W 1X5 – Tel. 647 554 8197 E-mail: torontofinote@gmail.com


# ፍኖተን እንደግፍ

ትክክል መረጃ ዜና ዘጋቢያችሁ

በየቀኑ አለ ፍኖተ ድምጻችሁ::

ሳምንታዊ ዜና ተንታኝ አቅራቢያችን

ፍካሬ ዜና አለ ምንም አያመልጠን።

ከታሪክ ማህደር መርጦ የሚያስተምረን

ፍኖተ እኮ ነው ሀቁን የሚነግረን።

ከሙዚቃ ጉዋዳ ከመጻህፍት ዓለም

በየፈርጁ አቅራቢ እንደ ፍኖተ የለም

ከመድበለ ግጥም መግለጫና ሀተታ

ጊዜውን ጠብቆ ሁለንም በተርታ

ከደብዳቤዎች ዓምድ የልብን ትርታ

ፍኖተ ያቀርባል ጠዋትና ማታ።

ፍኖተ ህያው ነው የዚያ ትውልድ ትውፊት:

የሰማዕታት ድምጽ የጀግኖቹ ውጤት።

ለህግ የበላይነት ለዲሞክራሲ መብት

ለኢ/ያ ነጻነት ለህዝብ እኩልነት

ድምጹን ያስተጋባል ፍኖተ ካለበት።

ይጠንክር ይጎልብት ለሃገር ህልውና;

የአንድነት ምሰሶ የኢትዮጵያ ነውና፣

ዛሬም እንደበፊት ድጋፍ ይሻልና:

ወገን ተረባረብ ብዙ ይቀራል ገና

ሳተላይ ሬዲዮ ቲቪውም አለና

ድጋፍህን አሳይ በሁሉም ቀጠና።

የህዝብ ድምጽ ነው ከቶ የማይቋዋረጥ:

የወገን አለኝታ ጠላትን አንቀጥቅጥ።

በድምጽም በምስልም ከህዝቡ ለመድረስ

ቆራጦችን እናግዝ በትጋት እንገስግስ

ላልሰማው አሰማ የተኛውን ቀስቅስ።

በሙያም፡ በቴክኒክ፡ በገንዘብ፡ በመላ:

በምትችለው መንገድ በመግዛት ቶምቦላ፣

ድጋፍ አሰባስቡ ሃሳብ አምጡ ሌላ።

በዓለም ዙሪያ ሁሉ  ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ

ፍኖተን እናድምጥ ፍኖተን እንደግፍ።

ክብር ምስጋና ለፍኖተ ዲሞክራሲ የኢ/ያ አንድነት
ድምጽ የሳተላይት ሬዲዮ አዘጋጆችና አቅራቢዎች